## የዘምዘም ባንክ አክስዮን ማኅበር

## መተዳደሪያ ደንብ

እኛ የዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማኅበር (ከዚህ በኋላ "ባንክ" የተባለ ሊጠራ የሚችል) መሥራቾች በኢትዮጵያ ሕግ በተለይም በ1952 በወጣው የንግድ ሕግ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1159/2019 እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት የባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ አካል የሆነውን ይህን መተዳደሪያ ደንብ ተስማምተንበት አጽድቀናል::

### አንቀጽ አንድ
### አክሲዮኖች

1. የባንኩ አክሲዮኖች በያንዳንዱ ባለአክሲዮን ሥም የተመዘገቡ፣ የማይከፋፈሉና እኩል ዋጋ ያላቸው ተራ አክሲዮኖች ናቸው::
2. አንድ አክሲዮን ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሕጋዊ ሰዎች በጋራ ሊያዝ የሚችል ሲሆን አፈጻጸሙም በንግድ አንቀጽ 328 መሠረት ይሆናል::
3. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ ይኖረዋል::
4. እያንዳንዱ አክሲዮን የተጻፈበት ዋጋ የሚኖረው ሲሆን፣ አክሲዮኖች ከተጻፈባቸው ዋጋ በላይ (በኘሬሚየም) ሊወጡ (ለሽያጭ ሊቀርቡ)ይችላሉ::
5. አንድ ባለአክሲዮን ሲሞት አክሲዮኖቹ ለሕጋዊ ወራሾቹ ይተላለፋሉ::

### አንቀጽ ሁለት
### የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1. በንግድ ሕጉ ቁጥር 331 መሠረት ተፈላጊ የሆነውን መረጃ የያዘ የባለአክስዮኖች መዝገብ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል:: ባለአክሲዮኖችም ያለክፍያ መዝገቡን ሊመለከቱት ይችላሉ::
2. ባለአክስዮን ያልሆኑ የተለያዩ አካላት መዝገቡን በባንኩ የሥራ ሰዓት የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በመገኘት ያለ ምንም ክፍያ ማየት ይችላሉ::
3. የባንኩ አስተዳደር በመዝገቡ ውስጥ ጉድለት (ስሕተት) መኖሩን ያወቀ እንደሆን በሠላሣ ቀናት ውስጥ እንዲስተካከል/እንዲታረም ማድረግ ይኖርበታል::

## አንቀጽ ሦስት
## የአክሲዮን ሰርቲፊኬት

1. ባንኩ የአክሲዮን ሰርቲፊኬቶችን አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች የሚያድል ሲሆን፣ ይህ ግን የሚፈፀመው ገንዘብ ለተከፈለባቸው አክሲዮኖች ብቻ ነው:: ሰርተፊኬቶቹ ቢያንስ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 330 ውስጥ የተገለጹትን ነገሮች ይይዛሉ፤ ቁጥርም ይሰጣቸዋል::
2. እያንዳንዱ የአክስዮን ሰርቲፊኬት ታትሞ፣ በዳሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ተፈርሞ እና የባንኩ ማህተም ተደርጎበት ባለአክሲዮኑን በማስፈረም ይሰጣል::
3. የአክስዮን ሰርቲፊኬት ለመለየት በሚያዳግት መልኩ በሚበላሽበት ጊዜ ወይም በሚጠፋበት ጊዜ ወደፊት ቦርዱ በሚወስነው መሠረት ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ሰርቲፊኬቱ እንዲተካ ማድረግ ይቻላል::

## አንቀጽ አራት
## የባለአክሲዮን መብቶች እና ግዴታዎች

1. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ቀጥሎ የተዘረዘሩት መብቶች ይኖረዋል:-
   - 1.1 በስሙ በተመዘገቡ አክስዮኖች መጠን በማኅበር ጉባዔዎች ላይ የመካፈል፣ ድምፅ የመስጠት፣ ድምፅ የመቀበል፣ የማኅበሩን ውሳኔ የመቃወም፤
   - 1.2 ከባንኩ ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ የመካፈልና እንዲሁም ባንኩ ሲፈርስ ከዕዳ ከሚተርፈው ቀሪ ገንዘብ ድርሻን የመካፈል፤
   - 1.3 የባንኩን የተለያዩ ውሣኔዎች የመጠየቅና የማግኘት፤
   - 1.4 ለባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ዕጩ ሆኖ የመቅረብ፤
   - 1.5 ባንኩ አዲስ አክሲዮኖችን ሲያወጣ (ሲሸጥ) ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው ጣሪያ ክልል በያዛቸው አክስዮኖች ድርሻ ልክ ለመግዛት ቅድሚያ የማግኘት፤
   - 1.6 በንግድ ሕጉ እና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አክሲኖቹን ለሌላ ወገን መሸጥ፣ ማስተላለፍ፣ ማስያዝ እና የአባል ጥቅም የማግኘት::
2. የአንድ ባለአክሲዮን ጥቅም ከባንኩ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ከሆነ ባለአክሲዮኑ በድምጽ መስጠት መብቱ አይጠቀምም::

## አንቀጽ አምስት

## አክሲዮን ስለማስተላለፍ

1. አክሲዮኖችን በንግድ ሕጉ መሠረት ያለምንም ገደብ ለሌላ ወገን ለማስተላለፍ የሚቻለው በንግድ ሕጉ ቁጥር 333 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ እና የባንኩ የዴሬክተሮች ቦርድ የፈቀደ እንደሆነ ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ እንደተጠበቀ ሆነ የተጽዕኖ ፈጠሪ ባለድርሻዎች አክሲዮኖች ዝውውር ከዳይሬክተሮች ቦርድ በተጨማሪ የብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ያስፈልገዋል።
3. ባለአክስዮኖችና ባንኩ ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፉ የቀረቡ አክስዮኖችን በቅድሚያ የመግዛት መብታቸው እንደተጠበቀ ነው።
4. የአክሲዮኖች መተላለፍ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ካልተመዘገበ ውጤት አይኖረውም።

## አንቀጽ ስድስት

## የተፈረሙ አክሲዮኖች ተከፍለው ስለሚጠናቀቁበት ጊዜ

1. ማንኛውም የባንኩ ባለአክሲዮን የፈረመውን አክሲዮኖች ባንኩ ፈቃድ ካገኘበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ማጠናቀቅ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መከፈል የሚገባውን አክሲዮኖች ከፍሎ ያላጠናቀቀ ባለአክሲዮን የሚኖር ከሆነ ባለአክሲዮኑ የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዲወጣ ማስጠንቀቂያ የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲሁም ባለአክሲዮኑ የሚጠበቅበትን ግዴታ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነ ያልተከፈሉት አክሲዮኖች ስለሚሸጡበት ሁኔታ አስመልክቶ የንግድ ሕግ አንቀጽ 342 ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ ሰባት

## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩ ከፍተኛ የአመራር አካል በመሆኑ ውሳኔዎቹ በንግድ ሕጉ ቁጥር 388 መሠረት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ አስገዳጅነት አላቸው።

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ "መደበኛ" ወይም "ድንገተኛ" ሊሆን ይችላል።

2. ጠቅላላ ጉባዔ በዲሬክተሮች ቦርድ፣ በኦዲተሮች፣በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲሁም እንደተገቢነቱ በሂሣብ አጣሪዎች ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ የሚያስፈልግ መሆኑን በማስረዳት የባንኩን አክሲዮኖች አሥር በመቶ (10%) የያዙ ባለአክስሲዮኖች ሲጠይቁ ፍርድ ቤት በሰየመው ዳኛ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. አንድ ባለአክሲዮን በሥሙ ድምፅ እንዲሰጥለት በአግባቡ በጽሑፍ ሥልጣን በሰጠው ወኪል አማካይነት በጠቅላላ ጉባዔ ድምጽ መስጠት ይችላል፡፡ ተወካዩ ባለአክሲዮን ላይሆንም ይችላል፡፡
4. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚደረገው ጉባዔው ከሚደረግበት ቀን አሥራ አምስት (15) ቀን በፊት በባለአክስዮኖች አድራሻ ከስብሰባው አጀንዳ ጋር በሪኮማንዴ በሚላክ ደብዳቤ ወይም በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ይሆናል፡፡
5. በባለአክሲዮኖች ወይም በወኪሎቻቸው በአግባቡ የሚፈረም በእያንዳንዱ ጉባዔ የተገኘ አባላት ዝርዝር ለእያንዳንዱ ጠቅላላ ጉባዔ ተዘጋጅቶ ይቀመጣል፡፡ ዝርዝሩም በጉባኤው ጽሕፈት ቤት ይረጋገጣል፡፡
6. ጠቅላላ ጉባዔዎች በቦርዱ ሰብሳቢ ይመራሉ፡፡ የቦርዱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ የቦርዱ ሲኒየር ዳይሬክተር ጠቅላላ ጉባዔዎችን ይመራል፡፡
7. ከፍተኛ አክሲዮን የያዙ ባለአክሲዮኖች የጠቅላላ ጉባዔ ድምጽ ተቀባዮች ወይም ቆጣሪዎች ሆነው ይመደባሉ፤
8. ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ የተደረጉ ወይይቶችና ክርክሮች በንግድ ሕግ ቁጥር 411 እና 412 መሠረት በሚዘጋጅ ቃለ ጉባዔ ተመዝግበው እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡
9. የቃለ ጉባዔ ቅጂዎች ወይም ግልባጮች በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም በሁለት ዲሬክተሮች የተረጋገጡና በጉባዔው በአብዛኛዎች የጽህፈት ቤት አባሎች የተፈረሙ መሆን አለባቸው፡፡

## <u>አንቀጽ ስምንት</u>
## <u>መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ</u>

1. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል፡፡ በጉባዔውም የሚከናወኑት ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

   1.1. የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ እንዲሁም የቦርዱንና የኦዲተሮች ሪፖርቶች ማጽደቅ፣

   1.2. በትርፍ አመዳደብና ክፍፍል እንዲሁም ካለፈው የሂሣብ ዓመት ጋር ተያይዞ በሚነሱ የሂሣብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት፣

1.3. የቦርዱን አባላትና የውጭ ኦዲተሮችን መሾም ወይም መሻር፣ ተግባርና ሥልጣናቸውን እንዲሁም የሚከፈላቸውን የሥራ ዋጋ መጠን መወሰን፣

1.4. ለድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከተሰጡት ተግባራት በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሁሉ ውሳኔ መስጠት፣

2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የሚካሄደው ከባንኩ የሂሣብ ዓመት መጨረሻ ቀን ጀምሮ ባለው የስድስት ወራት ጊዜ ወስጥ ነው::

3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መጀመሪያ ሲጠራ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክስዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛውን (25%) የያዙት ባለአክስስዮኖች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

4. ጉባዔው ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠራ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክስዮኖች ቁጥር ሳይታሰብ ጉባዔው ሊደረግና ወይይትም ሊካሄድ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. ጉባዔው ውሳኔ የሚሰጠው ተራ በሆነ የድምጽ ብልጫ ነው:: ለድምጽ አቆጣጠር ድምጽ ተዐቅቦና ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ካሉ ግምት ውስጥ አይገቡም::

## አንቀጽ ዘጠኝ
## ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ

1. ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን በማናቸወም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፣ በጉባዔውም ከሚከናውኑት ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

    1.1. የባንኩን መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፣

    1.2. የባንኩን መጠባበቂያ ሂሣብ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ካፒታል በማዞር የባንኩን ዋና ገንዘብ መጨመር፣

    1.3. ባንኩን ለማፍረስ በስምምነት መወሰን፡፡

2. በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የሚሰጠው ድምጸ ተዐቅቦ እና ድምጽ ያልተጻፈባቸው የጽምድ መስጫ ወረቀቶች ካሉ ከግምት ወስጥ ሳይገቡ ቁጥራቸው ከሁለት ሶስተኛ የማያንስ ባለአክስዮኖች ውሳኔውን ሲደግፉት ነው::

3. የባንኩን ዜግነት፣ የባንኩን ከወለድ ነፃ አላማ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመለወጥ፣ እንዲሁም ባለአክስዮኖች የዋና ገንዘብ ኢንቨስትሜንታቸውን (ካፒታል) እንዲጨምሩ ለማድረግ የተጠራው ድንገተኛ ጉባዔ የድምጽ መስጠት መብት



Documents Authentication & Registration Agency (Branch Ten Office)
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ያላቸውን ጠቅላላ አክስዮኖች መሰብሰብና ውሳኔዎቻቸውም ባንድ ቃል የተሰጡ እንዲሆኑ አስፈላጊ ነው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው በስተቀር ሌሎች ውሳኔዎች ለማስተላለፍ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘረው ሁኔታ መገኘት አለባቸው፡-

4.1. በመጀመሪያ ስብሰባ፣ ድምፅ ለመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች ከግማሽ የማያንሱ፤

4.2. በሁለተኛ ስብሰባ፣ ድምጽ ለመስጠት መብት ካላቸው ባለአክስዮኖች ከአንድ ሦስተኛ የማያንሱ፤

4.3. በሦስተኛ ስብሰባ፤ ድምፅ ለመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች ከአንድ አሥረኛ የማያንሱ፤

## <u>አንቀጽ አሥር</u>

## <u>የዲሬክተሮች ምርጫ</u>

1. ዲሬክተሮች በመመሥረቻ ጽሑፉ አንቀፅ 14.2 መሠረት ለሦስት አመታት ለማገልገል ይመረጣሉ፡፡
2. አግባብ ያላቸው የኢትዮጵያ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዲሬክተሮች በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሠረት በሥራ ዘመናቸው መጨረሻ እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡
3. የባንኩን ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ቢያንስ የሥራ ዘመናቸውን ከፈጸሙት ዲሬክተሮች መካከል ከሦስት አንድ እጅ (1/3) በድጋሚ ሊመረጡ ይችላል፡፡
4. ዲሬክተሮች ከመካከላቸው አንድ ሰብሳቢና አንድ ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡
5. የቦርዱ ሰብሳቢ የቦርዱን ስብሰባዎች ሁሉ ይመራል፣ እሱ ከሌለ ምክትል ሰብሳቢው ስብሰባውን ይመራል፡፡ ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው የሚመረጠው ዴሬክተር ስብሰባውን ይመራል፡፡
6. የዲሬክተሮች ቦርድ የራሱን ፀሐፊ ይመርጣል፡፡ የሚከፈለውንም የሥራ ዋጋ ይወስናል፡፡
7. ፀሐፊው በጉባዔው ላይ የመገኘት ማስረጃ ወረቀት /አቴንዳንስ ሺት/ ያዘጋጃል፡፡ ሕግ የሚጠይቃቸውን ቃለ ጉባዔዎች ይይዛል፡፡ ተገቢ ለሆነው የመንግስት ባለሥልጣን ምስጢር ያለባቸውን ደብዳቤዎች ያደርሳል፡፡ ፀሐፊው ባለክሲዮን ላይሆን ይችላል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ

## በባንኩና በዳሬክተሮች መካከል ስለሚደረጉ ግንኙነቶች

1. በባንኩና በማንኛውም ዲሬክተር መካከል ወይም፤ በባንኩና የባንኩ ዲሬክተር ባለቤት፣ የመጀመሪያ ደረጃ የቤተሰብ አባል፣ ወኪል፣ ዲሬክተር ወይም ሥራ አስኪያጅ በሆነበት በማንኛውም ድርጅት መካከል የሚደረግ ማናቸውም ግንኙነት በቅድሚያ በቦርዱ መጽደቅና ኦዲተሮችም እንዲያውቁት መደረግ እና መፈቀድ ይኖርበታል።
2. ማንኛውም ዲሬክተር ለቦርዱ የሚቀርብ የግል ጉዳይ ቢኖረው፤ በጉዳዩ ላይ ለመምከር በሚደረግ ስብሰባ ላይ የመሳተፍ እና ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም።

## አንቀፅ አሥራ ሁለት

## የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በባንኩ ዋና መ/ቤት ወይም በማናቸውም ቦርዱ በሚወስነው ሌላ ቦታ ሊደረግ ይችላል።
2. ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሆነ ዲሬክተሮች ሲገኙ ነው። እያንዳንዱ ዲሬክተር አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል።
3. አንድ ዲሬክተር የእሱን ሥራና ኃላፊነት በሚመለከት ጉዳይ ድምፅ አይሰጥም።
4. ዳይሬክተሮች የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ ላይ ጥሪ ማድረግ ሳያስፈልግ በስብሰባው ላይ መገኘት አለባቸው።ሆኖም ስብሰባው የቦርዱ ድንገተኛ ስብሰባ በሚሆንበት ጊዜ ለቦርዱ አባላት በሰብሳቢው ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው ጥሪ ያደርጋል ። ጥሪ የሚደረገውም የስብሰባውን አጀንዳ በማያያዝ ለዲሬክተሮች በሙሉ በሚደርስ ዘዋሪ የፅሑፍ ማስታወቂያ ይሆናል።
5. የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ ስብሰባዎችን ይመራል። ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ የስብሰባው ሰብሳቢ በተገኙት ዲሬክተሮች ይመረጣል።
6. የዲሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሰብሳቢው እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

7. አንድ ዲሬክተር ከስብሰባ የሚቀር ከሆነ በጽሑፍ ሌላውን በስብሰባው ላይ የሚገኝ ዲሬክተር ብቻ ሊወክል ይችላል፡፡ አንድ ዲሬክተር ሊወከል የሚችለው ለአንድ ዲሬክተር ብቻ ነው፡፡
8. ውሳኔዎች የሚያልፉት ፍፁም በሆነ የድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡
9. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባዔ ተፅፈው በዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ና በቦርዱ ጸሐፊ ይፈረማሉ፡፡ ቃለጉባዔውም ለዚሁ በተዘጋጀ መዝገብ ውስጥ ይቀመጣል፡፡ የውሳኔዎችም ቅጅዎች ንዲሁ በቦርዱ ሊቀመንበር ና በጸሐፊው መፈረም አለባቸው፡፡
10. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት ደንብ ያወጣል፡፡ እኩል በሚሆኑበት ጊዜ የቦርድ ሊቀመንበር ያለበት ድምፅ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀፅ አሥራ ሦስት
## የዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ግዴታዎች

1. የዲሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማኀበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ፣ በመተዳደሪያ ደንቡና በጉባዔው ውሳኔዎች የተሰጡትን ሥልጣንና ግዴታዎች ይፈጽማል፡፡

2. የዲሬክተሮች ቦርድ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡
   2.1 የባንኩን ሥራ ይመራል፡፡
   2.2 ከጠቅላላ ጉባዔው በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የማኀበሩ ዓላማ ግቡን እንዲመታ አስፈላጊና ሕጋዊ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳል፡፡
   2.3 የባንኩን ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤ የመምሪያ ኃላፊዎችን እንዲሁም የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች ይሾማል፡፡ ደመወዛቸውን ይተምናል፡፡ ማትጊያን፣ ሰንብትንና ፕሮቪደንት ፈንድ በሚመለከት ይወስናል፡፡
   2.4 የባንኩን የማይንቀሳቀሱም ሆነ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ይገዛል ይሻጣል፡፡
   2.5 የብድርና የመያዣ ውሎችን ይዋዋላል፡፡
   2.6 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን መሠረት አድርጎ በኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ የባንኩ ቅርንጫፎች እንዲከፈቱ ይወስናል፡፡
   2.7 ተገቢ/ ጠቃሚ የመሰለውን ሀሳብ የባንኩን ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግን ጨምሮ፣ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡
   2.8. ቦርዱ ሥራውን የሚያከናውንበት የሥነስረዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

3. ዴሬክተሮቹ በባንኩ ሥራ አስኪያጅነት ወይም ወኪልነት የጋራ ኃላፊነት አለባቸው::

## አንቀፅ አሥራ አራት
## የዲሬክተሮች አበልና የሥራ ዋጋ

ለዴሬክተሮች የሚደረገው አበልና የሥራ ዋጋ ክፍያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው መመሪያ ላይ በተመለከተውና ወደፊትም በዚሁ ጉዳይ ላይ በሚወጡ መመሪያዎች ላይ ተመስርቶ በጉባኤው ተወስኖ ይፈፀማል::

## አንቀጽ አሥራ አምስት
## የዲሬክተሮች መለወጥና መነሳት

1. ዲሬክተሮችን በቋሚነት የመሰየም፣ የመቀየር፣ ቁጥራቸውን የመጨመርና የመቀነስ ሥልጣን የጠቅላላ ጉባዔው ነው::
2. በሁለት ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች መካከል አንድ ወይም ብዙዎች ዲሬክተሮች በማንኛ ውም ምክንያት የጎደሉ እንደሆነ በንግድ ሕጉ ቁጥር 351 መሠረት:-

   2.1 ሥራ ላይ ያሉት ዲሬክተሮች የጎደሉትን ዲሬክተሮች ምትክ ተጠባባቂዎች መርጠው ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ አቅርበው እንዲጸድቅ ያደርጋሉ:: ጉባዔውም እነዚህን ሊያጸድቅ ወይንም ሌሎችን ሊመርጥ ይችላል::
   2.2 ሆኖም የቀሩት የዲሬክተሮች ቁጥር ከአባላቱ ከግማሽ በታች ከሆነ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ ምርጫ ይካሄዳል::
   2.3 እንዲሁም ሁሉም ዲሬክተሮች ሥራቸውን የተው እንደሆነ ኦዲተሮች አስቸኳይ ጉባዔ ጠርተው ያስመርጣሉ፤እስከዚያ ግን የአስተዳደር ሥራዎችን መፈጸም ይችላሉ::
3. በአንድ ዲሬክተር ምትክ ሌላ የሚተካው:-
   1.1 ለቦርዱ በጽሑፍ በማስታወቅ የዲሬክተርነቱን ሥራ ሲለቅ፤ ወይም
   1.2 የቦርዱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ባለማክበር ወይም በሌላ ጥፋት ምክንያት ሲቀጣ፤ ወይም

1.3 በሞት ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሲለይ ነው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

## የሸሪዓ አማካሪዎች ሥልጣንና ተግባር

1. የባንኩ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በወለድ ላይ ያልተመሠረት የባንክ አሠራር መርህን የተከተለ እንዲሆን ቦርዱን ማማከር፡፡
2. በወለድ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ አሰራር መመሪያዎች፣ አገልግሎቶች፣ ውሎች፣ እንዲሁም ሌሎች የባንኩ አሰራሮች በወለድ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ አሰራር መርህን የተከተሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
3. ባንኩ የሚሰጠውን በወለድ ላይ ያልተመሠረተ አገልግሎት በተመለከተ ከደንበኞች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መቀበልና እንደ አግባብነቱ መልስ እንዲሰጥባቸው ማድረግ፡፡
4. በወለድ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ አሠራርን በተመለከተ ከኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር መመካከር፡፡
5. የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሸሪዓ አማካሪዎች ስለሚኖረው ተጨማሪ ሥልጣንና ተግባር በየጊዜው ሊወስን ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት

## የዋናው ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

1.ዋናው ሥራ አስፈጻሚ ከዲሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ፣ በመመሥረቻቸው ጽሁፍ፣ በመተዳደሪያው ደንብና አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የባንኩን ሥራ ያካሂዳል፡፡

2.ዋናው ሥራ አስፈጻሚው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ. የባንኩን የየዕለት ሥራዎች መምራት፣

ለ. የቦርዱን ወሳኔዎች ተግባራዊ ማድረግ፣

ሐ. የባንኩን መምሪያ ኃላፊዎችና ወኪሎች ሹመት እንዲሁም ደሞዝና አበላቸውን ቦርዱ እንዲያፀድቀው ማቅረብ፣

መ. የባንኩን የውስጥ ደንብ በማዘጋጀት ቦርዱ እንዲያፀድቀው ማቅረብና ቦርዱ

ካፀደቀው በኋላ ሥራ ላይ ማዋል፤

ሠ. በሕግና በባንኩ የውስጥ ደንብ መሠረት የባንኩን ሠራተኞች መቅጠር፣ ማስተዳደር ወይም ማሰናበት፤

ረ. ባንኩን በፍርድ ቤትና በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ዘንድ መወከል እንደ አስፈላጊነቱም ውክልና ለባለሙያ መስጠት፤

ሰ. በቦርዱ መመሪያ መሠረት የባንኩን ሂሳብ መክፈትና ማንቀሳቀስ፤

ሸ. በባንኩ የውስጥ ደንብ መሠረት እንደ ቼክና የሐዋላ ወረቀት ያሉ የንግድ ሰነዶችን ማውጣት፣ መፈረም፣ መቀበልና ማስተላለፍ፤

ቀ. ቦርዱን በጽሁፍ በማስፈቀድ ከሌሎች ባንኮች በዋስትና ወይም ያለዋስትና ያለወለድ ገንዘብ መበደር፤

በ. የባንኩ የውስጥ ደንብ ከፈቀደው ገደብ ሳያልፍ ያለወለድ ገንዘብ ማበደር፣ አድቫንስንና የኦቨርድራፍት ብድር መስጠት፤

ተ. የባንኩን ሂሳቦችና ሌሎች መዛግብት በሕጉና በተለመደው የንግድ አሰራር መሠረት መያዝ ወይም እንዲያዙ ማድረግ፤

ቸ. የሂሳብ ዓመቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከሁለት ወር በፊት የባንኩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ማዘጋጀትና ቦርዱ እንዲያፀድቀው ማቅረብ

ኀ. የሥራ ክንውን ሪፖርት በየሶስት ወሩና የሂሳብ ሪፖርት በየዓመቱ ለቦርዱ ማቅረብ

ነ. ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የባንኩን የህብረት ስምምነት ተደራድሮ መፈረም፤

ኘ. ቦርዱ በሚፈቅደው መሠረት የባንኩን ቅርንጫፍ መክፈት፣ መዝጋት፤

አ. ለባንኩ የተቀላጠፈ አመራር ያስፈልጋል ብሎ ካመነ ሥልጣኑንና ተግባሩን ከፍሎ ለባንኩ ሰራተኞች በውክልና መስጠት፤

ከ. ዲሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ

## የውጭ ኦዲተሮች

1. የውጭ ኦዲተሮች በመጀመሪያው የባንኩ ቦርድ ተሹመው ለአንድ ዓመት ይሠራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ኦዲተሮች በጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ ለሦስት ዓመታት የሚሾሙ ይሆናል፡፡
2. ይሁንና በማሕበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ከመቶ ሀያ (20%) ያላነሰ ድርሻ የያዙ ባለአክሲዮኖች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የራሳቸውን ተጨማሪ ኦዲተር መመደብ ይችላሉ፡፡

3. የተጨማሪ ኦዲተሮችን የሥራ ዋጋና አበል በሚመለከት ባንኩ በከፊል ወይም በሙሉ ይከፍል እንደሆነ ጠቅላላ ጉባዔው ይወስናል።

4. ኦዲተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩዋቸዋል፡-

    4.1. የባንኩን መዛግብትና የገንዘብ ዋስትና ሰነዶችን መመርመር፤

    4.2. የባንኩ ንብረት በትክክል ተመዝግቦ መያዙን፣ መተዳደሩንና መጠበቁን፣ እንዲሁም የሂሣብ ሚዛኖች እና የትርፍና የኪሣራ መግለጫዎች በትክክል መሠራታቸውን ማረጋገጥ፤

    4.3. ስለ ባንኩ ሁኔታ ቦርዱ ያቀረበው ሪፖርት ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ፤

    4.4. ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ማቅረብ፤

    4.5. ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ለቦርዱ እና/ወይም ለጠቅላላ ጉባዔው ማሳወቅ፣ እንዲሁም ወንጀል መፈጸሙን ሲረዱ / የዕርማት እርምጃ መውሰድ፣ ማስተማር፣ ማስጠንቀቅ/ ለብሔራዊ ባንክና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ማስታወቅ፤

    4.6. በሕጉ ወይም በመመሥረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቦርዱ ጠቅላላ ጉባዔውን ካልጠራ መጥራት፤

    4.7. የባንኩን የፋይናንስና የሥራ አመራር በሚመለከት በማንኛውም ጊዜ ድንገተኛ ምርመራ ማካሄድ እና

    4.8. በጠቅላላ ጉባዔ እና በቦርዱ የሚሠጧቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት መፈፀም።

## አንቀጽ ሃያ

## የትርፍ ድርሻና መጠባበቂያ ሂሣብ

1. የባንኩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የትርፍ ድርሻ አስመልክቶ ይወስናል።
2. የትርፍ ድርሻዎች ሊከፈሉ የሚችሉት በጠቅላላ ጉባኤው በጸደቀው የሂሣብ ሚዛን ላይ ከሚታየው የተጣራ ትርፍ ላይ ብቻ ነው።
3. ባንኩ በማናቸውም የትርፍ ድርሻ ላይ ወለድ እንዲከፍል አይጠየቅም።

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## የካፒታል መጨመር

1. የባንኩን ካፒታል አዲስ አክሲዮን በማውጣት ወይም ያሉትን አክስዮኖች ዋጋ በማሳደግ መጨመር ይቻላል።

Federal Documents Authentication and Registration Agency Addis Ababa Branch Ten Office

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 10

2. ካፒታል እንዲጨምር የሚወሰነው በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን ጭማሪው የሚከፈለው ጉባዔው በሚወሰነው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
3. የአዲስ አክሲዮኖች አመዳደብ በንግድ ሕግ ቁጥር 470 እስከ ቁጥር 472 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡
4. ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤው አዲስ አክሲዮኖች ለሕዝብ እንዲሸጡ መወሰን ይችላል፡፡
5. በንግድ ሕጉ ቁጥር 482 እና 483 የባንኩን መጠባበቂያ ሂሣብ ወደ ካፒታልነት ስለመለወጥ የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት
## የባንኩ ሂሣብ

1. ባንኩ በንግድ ሕጉ በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፣ በየሂሣብ ዓመት መጨረሻም የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ያዘጋጃል፡፡
2. ባንኩ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ዋና ካፒታሉን እስኪያህል ድረስ በየዓመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ ከመቶ ሀያ አምስት (25%) እያነሳ ወደዚሁ መጠባበቂያ ሂሣብ ያስተላልፋል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ማቋቋም ይችላል፡፡
4. የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የዲሬክተሮች ቦርድና የኦዲተሮች ሪፖርቶች ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባሉ፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሦስት
## ስለመፍረስና ሂሣብ ማጣራት

1. ባንኩ ስለሚፈርስበት ሁኔታ የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና የንግድ ሕጉ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. የሂሣብ አጣሪዎች ሹመት፣ ሥልጣንና ተግባር በንግድ ሕጉ ከቁጥር 496 እስከ 509 በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት
## የባንኩ ማኅተም

ቦርዱ የባንኩ ማኅተም በጥንቃቄ እንዲያዝ ያደርጋል፣ ማኅተሙም የሚደረግበት ማናቸውም ሰነድ ሥልጣን በተሰጠው የባንኩ የሥራ መሪ ይፈረማል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## መመሥረቻ ጽሑፉንና መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል

1. መመሥረቻ ጽሑፉንና መተዳደሪያ ደንቡን በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማሻሻል ይቻላል፡፡
2. የባንኩን ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ በሆኑ ሥራዎች ላይ ብቻ የመሠማራት ዓላማን መቀየር የአባላትን ሙሉ በሙሉ መስማማትን ይጠይቃል፡፡
3. የመመሥረቻ ጽሑፉንና መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል ከቁጥር 462 እስከ 494 ያሉት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

## ስለ ቋንቋ

መመሥረቻ ጽሑፉና መተዳደሪያ ደንቡ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ሲሆን፣ በሁለቱ ቅጂዎች መካከል ግጭት ወይም ልዩነት ቢኖር የአማርኛው ትርጉም በበላይነት ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስምንት

## ተፈጻሚ ሕጎች

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ስላልተጠቀሱ ጉዳዮች የንግድ ሕጉ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች እዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

እኛ ዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማሕበር መሥራች ባለአክሲዮኖች ይህንን መተዳደሪያ ደንብ ለማጽደቃችን ማስረጃ ይሆን ዘንድ ከዚህ ሰነድ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ላይ ዛሬ ህዳር 06, 2012 ቀን የተለመደው ፊርማችንን አኑረናል፡፡

አዲስ አበባ

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa Branch Ten Office

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

# ዘምዘም ባንክ አ.ማ. (በምስረታ ላይ)

## የቦርድ አባላት

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ሀላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | ናስር ዲኖ በድሩ (ዶ/ር) | ሰብሳቢ | |
| 2 | ሁሴን አግራው ኢብራሂም | ም/ሰብሳቢ | |
| 3 | አህመድ ሁሴን ሠኢድ (ዶ/ር) | አባል | |
| 4 | እንድሪስ መሀመድ የሡፍ (ዶ/ር) | አባል | |
| 5 | ጀማል ሙዘይን መሀመድ | አባል | |
| 6 | መከነሠላም መሀመድ ነገዎ | አባል | |
| 7 | ለይላ ናስር ከማል | አባል | |
| 8 | ነዲም አብዱሠመድ ኢብራሂም | አባል | |
| 9 | ቢያ ሀጂ አብዱላ | አባል | |
| 10 | ኑረዲን መሀመድ ኢብራሂም | አባል | |
| 11 | ሰላሀዲን ከሊፋ አብዱልቃድር | አባል | |

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa (Branch Ten Office)